የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኤጀንሲ

የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ሪፖርት

የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኤጀንሲ የተመደበለትን የመደበኛና የካፒታል ሂሳብ በጀት ለታቀደለት ዓላማ ማዋሉን፣ እንዲሁም ሂሳቡ በመንግሥት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት መያዙንና የመንግሥት ሀብትና ንብረት በሚገባ መጠበቁን ለማረጋገጥ የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ሪፖርቶችን እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርገናል፡፡

የሂሳብ ሪፖርቶችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የኤጀንሲው ሥራ አመራር ሲሆን፣ የሂሳብ ሪፖርቶችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው::

ኦዲቱ የተከናወነው የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን ሲሆን፣ ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሠረት በማድረግ ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ላይ አጥጋቢ የሆነ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለናል፡፡ ኦዲታችን ፡-

- በሂሳብ መግለጫዎች ላይ የሰፈሩትን አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና ኦዲት ማከናወንን፣
- የሥራ አመራሩ የሂሳብ መግለጫዎችን ሲያዘጋጅ ያደረገውን ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎችን መመዘንን፣
- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ያጠቃልላል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦችና በተከታታይ የወጡ መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆኑን በናሙና ኦዲት ማከናወንን ይጨምራል::

የሂሳብ መግለጫዎች ጉልህ ከሆኑ ስህተቶች የፀዱ ለመሆኑ በቂ ማስረጃና አጥጋቢ ማረጋገጫ የሚሰጥ መረጃና ማብራሪያ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል፡፡

ለኦዲቱ ሥራ መሠረት የሆኑት ኤጀንሲው ያቀረባቸው የሂሳብ መግለጫዎች፣ መዛግብት፣ ደጋፊ ማስረጃዎች፣እንዲሁም በኦዲት ተደራጊው መ/ቤት ሥራ አመራር የተሰጡ ማብራሪያዎች ናቸው:: ኦዲቱ የተከናወነው የበጀት ዓመቱን የሂሳብ እንቅስቃሴ ሊወክሉ የሚችሉ ናሙናዎችን በመውሰድ በጥልቀትና በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው::

የሚከተሉት የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኤጀንሲ የሂሳብ መግለጫዎች ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዘው ቀርበዋል::

- የገቢ/የዕርዳታ/የብድር ሂሳብ ሪፖርት፣
- የወጪ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የተሰብሳቢ ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የተከፋይ ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የዝውውር ሂሳብ ሪፖርት፣
- የሂሳብ ሚዛን ሙከራ፣

ለኦዲት አስተያየቱ መሠረት የሆኑት ጉዳዮች፣

የኤጀንሲው የሂሳብ መግለጫዎች ጉልህ የሆነ ግድፈት የሌለባቸው፣ በአዋጅ በተፈቀደው በጀት እና በመንግሥት ሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት የተዘጋጁ እና የተሰበሰበው ገቢ፣ የተከፈለው ወጪና የበጀት አጠቃቀሙ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅን፣ ደንብና መመሪያን የጠበቁ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

ወጪ

1. በኤጀንሲው በመምህርነት ከተቀጠሩ የውጭ ሀገር ዜጎች ደመወዝ ተቀናሽ መደረግ የሚገባው የሥራ ግብር በድምሩ ብር 2,099,916.47 ሳይቀነስ ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል::
2. የተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 2,093,830.53 ተቀናሽ መደረግ ሲገባው፣ ብር 1,463,212.66 በመቀነሱ በልዩነት ብር 630,617.86 ተቀናሽ ሳይደረግ ለተቋራጩ የተከፈለ መሆኑን፣
3. በተለያዩ የክፍያ ምስክር ወረቀቶች ለህንፃ ተቋራጭ ክፍያ ሲፈፀም ተቀናሽ የተደረገ የመያዣ ሂሳብ ብር 1,162,363.60 በተከፋይ ሂሳብ አለመያዙን ለማወቅ ተችሏል::
4. በኤጀንሲው በማገልገል ላይ የሚገኙ የኒውዝላንድ ዜጋ የሰለጠኑበትን ሙያ እና የትምህርት ደረጃ የሚገልፅ ማስረጃ ሳይቀርብ በኤጀንሲው ተቀጥረው ከ2002 ዓ.ም ጀምሮ በመስራት ላይ የሚገኙ መሆኑንና በበጀት ዓመቱ በድምሩ ብር 886,096.58 አለአግባብ የተከፈለቸው መሆኑ ተረጋግጧል::

ተሰብሳቢ ሂሳብ፣

5. በተለያዩ የሂሳብ መደቦች በተሰብሳቢ የተያዘ በድምሩ ብር 1,242,981.64 በደንቡና በመመሪያው መሠረት በወቅቱ ሳይወራረድ ተገኝቷል::
6. በሂሳብ መደብ 4203 ብር 148,732.36 እንዲሁም በሂሳብ መደብ 4253 ብር 3,721,426.36 በተቀፅላ የሂሳብ ቋት (ሌጀር) ባልተለመደ የሂሳብ ሚዛን (ክሬዲት) ተመዝግቦ መገኘቱ ታውቋል::

ተከፋይ ሂሳብ

7. በተለያዩ የሂሳብ መደቦች በተከፋይ የተያዘ በድምሩ ብር 6,761,315.61 ለባለመብቶች ሳይከፈል ተገኝቷል፡፡
8. በተከፋይ የሂሳብ መደብ 5002 የተያዘ ብር 44,766.92 በተቀፅላ የሂሳብ ቋት (ሌጀር) ባልተለመደ የሂሳብ ሚዛን (ዴቢት) ተመዝግቦ መገኘቱ ተረጋግጧል።

በጀት፣

9. የካፒታል በጀት ብር 272,393.87 ከበጀት በላይ ወጪ መደረጉ ታውቋል።

ከላይ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 9 በተገለጹት ጉልህና መሠረታዊ ልዩነቶች የተነሳ በእኛ አስተያየት የኤጀንሲው የሂሳብ መግለጫዎች ሰኔ 30 ቀን 2009 ዓ.ም. የተመለከተውን የፋይናንስ አቋም እና የበጀት ዓመቱን የሥራ እንቅስቃሴ በኢትዮጵያ መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ እንዲሁም የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት በአጥጋቢ ሁኔታ አያሳዩም።

ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች

ቀጥሎ የተመለከቱት ጉዳዮች ትኩረት ሊደረግባቸው፣ እርምጃ ሊወሰድባቸው እና ለወደፊቱም ጥንቃቄ ሊደረግባቸው ይገባል።

- ከሚመለከተው አካል የሙያ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ባልተሰጣቸው በኤጀንሲው የምህንድስና ክፍል ሠራተኞች በተዘጋጀ የክፍያ የምስክር ወረቀት በድምሩ ብር 7,205,684.01 ለህንፃ ተቋራጭ ክፍያ የተፈፀመ መሆኑ ተረጋግጧል ።
- በድምሩ ብር 6,382,264.65 ወጪ በተደረገባቸው የባንክ ወጪ ማስመስከሪያዎች በየሂሳብ መደቦቹ ለተያዘው ወጪ በጀት መኖሩ በባለሙያ ሳይረጋገጥ ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል።
- በኤጀንሲው ለተቀጠሩ የውጪ አገር ዜጎች ደመወዝ ሲከፈል በባንክ ሂሳብ በማስተላለፍ ክፍያ መፈጸም ሲገባው በተለያዩ የወጪ ማስመስከሪያዎች ከብር 5,000.00 በላይ ከሣጥን ወጪ ሆኖ በድምሩ ብር 1,633,462.02 በጥሬ ገንዘብ ክፍያ ተፈፅሞ ተገኝቷል።
- ለመስተንግዶ የተከፈለ ብር 747,327.01 እንዲሁም የህትመት አገልግሎት ግዥ ለተፈፀመበት ወጪ የሆነ ብር 88,480.43 በድምሩ ብር 835,807.44 በ2008 በጀት ዓመት ለተከናወነ ግዥ ክፍያ ተፈፅሞ ተገኝቷል።
- በድምሩ ብር 2,329,079.70 በተገቢው የሂሳብ መደብ ሳይመዘገብ መገኘቱ ተረጋግጧል።
- የመደበኛ በጀት ብር 18,166,762.83 እንዲሁም የካፒታል በጀት ብር 111,634,928.30 ሥራ ላይ ያልዋለ መገኘቱን፣

- ብር 223,492.491 ዋጋ ያላቸውን ንብረቶች ሳይመልሱ የተረከቧቸው ሠራተኞች ኤጀንሲውን የለቀቁ መሆኑ ተረጋግጧል።

ሌሎች ጉዳዮች፣

- የሰሌዳ ቀጥሩ 4-15398 እና የሰሌዳ ቀጥሩ 4-15399 ቶዮታ ኮምፓክት መኪናዎች በብልሽት ምክንያት ለ1 ዓመት መቆማቸው፣እንዲሁም የሰሌዳ ቀጥር 4-15385 ቶዮታ ፒክ አፕ ለወራቶች ሳይሰራ መገኘቱን፣
- በቋሚ ንብረት ግምጃ ቤት ውስጥ ቋሚና አላቂ ንብረቶች ተቀላቅለው በአንድ መጋዘን ውስጥ የተቀመጡ መሆኑ፡፡

በ2008 ኦዲት ግኝቶች ላይ ስለተወሰደ የእርምት እርምጃ፣

- የኤጀንሲው ሠራተኞች ለመሠረታዊ የአሰራር ማሻሻያ (BPR)ሥልጠና በፊሊፒንስ ለቆዩበት ለእያንዳንዳቸው ለውሎ አበል ከተከፈላቸው ብር 368,320.01 በሚያቀርቡት የክፍያ ማስረጃ መወራረድ የሚገባው ብር 45,860.98 የወጪ ማስረጃ ሳይቀርብለት በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኤጀንሲ

የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት የሥራ አመራር ሪፖርት

መግቢያ፣

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን መሰረት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኤጀንሲ የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ላይ የኦዲት አስተያየታችንን ለመስጠት ያስችለን ዘንድ የኤጀንሲውን ሂሳብ ኦዲት አድርገናል፡፡

ዓላማ፣

የዚህ ሪፖርት ዓላማ በኦዲታችን ወቅት የተገኙትን የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች እና ሌሎች ግድፈቶች የኤጀንሲው የበላይ አመራር አካላት እንዲያውቁትና ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ በመውሰድ ምላሽ እንዲሰጡበት ለማስቻል ነው፡፡

የኦዲቱ ወሰንና ኃላፊነት፣

ኦዲቱ የተከናወነው ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሰረት በማድረግ ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች በመከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመስራት በተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ላይ አጥጋቢ የሆነ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለናል፡፡

ኦዲታችን ፣

- በሂሳብ መግለጫዎች ላይ የሰፈሩት አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና ኦዲት ማከናወንን፣
- የሥራ አመራሩ የሂሳብ መግለጫዎችን ሲያዘጋጅ ያደረጋቸው ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎች መመዘንን፣
- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ፣ያጠቃልላል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ለኦዲቱ የተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆናቸውን ኦዲት ማድረግን ይጨምራል፡፡

ቀጥለው በተመለከቱት የኦዲት ግኝቶች ላይ የማሻሻያ ሀሳቦችን ለመስጠት በሂሣብ መግለጫዎች ላይ ያለውን የመረጃ አቀራረብ አጠቃላይ ብቃት ገምግመናል፡፡

ይሁን እንጂ ኦዲቱ በኤጀንሲው የሚታዩትን የውስጥ ቁጥጥርና ሌሎች ድክመቶችን ሙሉ በሙሉ ሊያሳይ አይችልም፡፡

የሂሳብ መግለጫዎችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የኤጀንሲው ሥራ አመራር ሲሆን፣ የሂሳብ መግለጫዎችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው፡፡

የኤጀንሲው የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች ከዚህ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

1. **የወጪ ሂሳብ፣**

1.1.1 **ግኝት፣ በኤጀንሲው ሠራተኞች በተዘጋጀ የክፍያ ምስክር ወረቀት የተፈፀመ ክፍያ፣**

ሰኔ 2002 ዓ.ም በወጣው የፌዴራል መንግስት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ አንቀጽ 28.5 ፊደል ሀ መሰረት ለግንባታ ዘርፍ ስራ ክፍያ የሚፈጸመው የስራውን ደረጃ ተከትሎ ከአማካሪ መሐንዲሱ በሚሰጥ የክፍያ የምስክር ወረቀት መነሻነት ብቻ እንደሆነ ይገልጻል፡፡ በተጨማሪም ከፍተኛ ዋጋ በሚጠይቁና ውስብስብ ወይም ቴክኒካል የሆኑ ስራዎች በሙያው በቂ ዕውቀት ያላቸው የውጭ አማካሪዎችን በመቅጠር ማሰራት እንደሚገባ በመመሪያው ተመልክቷል፡፡ ይሁን እንጂ ለግንባታ ዘርፍ ስራዎች የተከፈሉ ክፍያዎችን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ኤጀንሲው የአጥር ግንባታ እና የተለያዩ የጥገና ሥራዎችን ለማሰራት ከተክላይ ግደይ የህንፃ ሥራ ተቋራጭ ጋር በብር 16,897,579.59 ውል የገባ ሲሆን በቀን 07/02/09 በባንክ ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 0832631 ብር 3,306,174.11፣ በቀን10/04/09 በባንክ ማስመስከሪያ ቁጥር 0831813 ብር 2,222,585.42 እንዲሁም በቀን 13/08/09 በባንክ ማስመስከሪያ ቁጥር 243938 ብር 1,676,924.48 በድምሩ ብር 7,205,684.01 ከሚመለከተው አካል የሙያ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ባልተሰጣቸው በኤጀንሲው የምህንድስና ክፍል ሠራተኞች በተዘጋጀ የክፍያ የምስክር ወረቀት ክፍያ የተፈፀመ መሆኑ ተረጋግጧል ፡፡

1.1.2 **ስጋት፣**

- *መንግሥት ያወጣቸው አዋጅ፣ ደንቦች እና የአፈፃፀም መመሪያዎች ሥራ ላይ እንዳይውሉ ሊያደርግ ይችላል፡፡*
- *ያለፈቃድ የማማከር አገልግሎት እንዲሰጥ መደረጉ ለሚደርሰው የሥራ ግድፈት ተጠያቂነት እንዳይኖር ሊያደርግ ይችላል፡፡*

1.1.3 **የማሻሻያ ሀሳብ፣**

ከፍተኛ በጀት የሚመደብለት የግንባታ ወጪ በግንባታ ሥራው ላይ ችግር ቢፈጠር ተጠያቂነትን እና ኃላፊነትን ሊወስድ በሚችል አካል ክትትል ሊደረግለት የሚገባ በመሆኑ መመሪያን የተከተለ አሰራር ተግባራዊ መደረግ ይኖርበታል፡፡

1.1.4 **የሥራ አመራሩ ምላሽ፣**

የሥራ አመራሩ የተሰጠውን የማሻሻያ ሀሳብ ተቀብሎታል፡፡

1.2.1 **ግኝት፣ በጀት ስለመኖሩ በኃላፊ ሳይረጋገጥ የተፈፀመ ክፍያ፣**

የፌዴራል መንግሥት የበጀት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 2/2003 አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 02 ተራ ቁጥር 1 ማንኛውም የመንግስት መሥሪያ ቤት ለበጀት ዓመቱ የተፈቀደለትን የመደበኛም ሆነ የካፒታል በጀት አጠቃቀም በሚገባ ለመቆጣጠር እንዲችል የበጀት መቆጣጠሪያ መዝገብ ወይም የተዘረጋ የኤሌክትሮኒክስ መረጃ ሥርዓት አመዘጋገብ ሊኖረው እንደሚገባ ያዛል። በተጨማሪም የፌዴራል መንግስት የፋይናንስ አስተዳደር ደንብ 190/2002 ክፍል 3 ተራ ቁ 12 የመንግሥት ገንዘብ ክፍያ ሊፈፀም ወጪ ሊደረግ የሚችለው የተፈቀደ በጀት ሲኖር ነው። ሲሆን በዚሁ መሠረት ቁጥጥሩ የሚደረግ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በድምሩ ብር 6,382,264.65 ወጪ በተደረገባቸው የባንክ ወጪ ማስመስከሪያዎች በየሂሳብ መደቦቹ ለተያዘው ወጪ በጀት መኖሩ በባለሙያ ሳይረጋገጥ ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል።

1.2.2 **ስጋት**

- ከተፈቀደ በጀት በላይ ክፍያ ሊፈፀም ይችላል፡፡
- መንግስት ያወጣውን ደንብና መመሪያ ያለመከተል ተጠያቂነትን ሊያስከትል ይችላል ፡፡

1.2.3 **የማሻሻያ ሀሳብ፣**

ወጪዎች ከመፈፀማቸው በፊት በጀት ስለመኖሩ በሚመለከተው ኃላፊ መፈረሙ መረጋገጥ ይኖርበታል፡፡በተጨማሪም የበጀት አፈፃፀሙን ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መንገድ ማስተዳደር እንዲቻል ክትትል እና ቁጥጥር ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡

1.2.4 **የሥራ አመራሩ ምላሽ፣**

የሥራ አመራሩ የተሰጠውን የማሻሻያ ሀሳብ ተቀብሎታል።

1.3.1 **ግኝት፣ከመምህራን ደመወዝ ተቀናሽ ያልተደረገ የሥራግብር፣**

በገቢ ግብር አዋጅ 979/2008 ዓ/ም ክፍል ሁለት አንቀጽ 9 ማንኛውም ገቢ የሚያገኝ ሰው በዚህ አዋጅና በታክስ አስተዳደር አዋጅ መሠረት ግብር የመክፈል ግዴታ እንዳለበት ያዛል። ይሁን እንጂ ኤጀንሲው በኮንትራት ውል በመቅጠር የሚያሰራቸውን የውጭ ሀገር ዜጎች ከግብር ነፃ መሆናቸውን የሚገልጽ ማስረጃ ሳይኖር በድምሩ ብር 2,099,916.47 ከመቀጠር የሚገኝ ገቢ ላይ የሥራ ግብር ሳይቀነስ ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል።

1.3.2 **ስጋት፣**

- ተቀናሽ መደረግ የሚገባው ግብር ለሚመለከተው አካል ገቢ ባለመደረጉ የመንግስት የገቢ አሰባበሰብ ሥርዐት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ሊያሳድር ይችላል።
- የወጣው የገቢ አሰባሰብ ደንብና መመሪያ ተግባራዊ ላይደረግ ይችላል።

1.3.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

ተቀናሽ መደረግ የሚገባው የሥራ ግብር ከሚመለከታቸው መምህራን ተመላሽ ተደርጎ ለግብር ሰብሳቢው ባለሥልጣን ገቢ መደረግ ይገባዋል፡፡ ለወደፊቱም በደንቡ መሠረት ተቀናሽ እንዲደረግ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል፡፡

1.3.4 <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

በቀረበልን የውል ስምምነት መሰረት ሰርተናል፡፡ ነገር ግን አግባብ አለመሆኑን አምነንበት የበላይ አመራሮች ይህን ጉዳይ እንደሚፈቱ ተነጋግረናል፡፡ በአሁኑ ሰዓት ግን የውጭ ዜጎች ቅጥር እና ክፍያ ከኤጀንሲው ወጥቶ ለTI (ቲአ) ኢንስቲትዩት የተሰጠ መሆኑን ለማረጋገጥ እንወዳለን፡፡

ሆኖም በተሰጠው የማስተካከያ ሃሳብ መሰረት ተቀናሽ መደረግ የሚገባው የሥራ ግብር ከሚመለከታቸው መምህራን ተመላሽ ተደርጎ ለግብር ሰብሳቢው ባለሥልጣን ገቢ መደረግ ይገባዋል፡፡ ለሚለው ሰራተኞች ወደ ሀገራቸው የተመለሱ በመሆኑ እና በመጀመሪያም ውሉ መስተካከል የሚገባው ስለሆነ ሳይቆረጥ የተከፈለውን የስራ ግብር ለማስመለስ አስቸጋሪ በመሆኑ እንዲታወቅ እንወዳለን፡፡ ነገር ግን ለወደፊቱም በደንቡ መሠረት ተቀናሽ እንዲደረግ ውሉም በዚሁ አግባብ እንዲያዝ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ እንዳለብን ተምረንበታል፡፡ (የሚታይ)

1.3.5 <u>የኦዲተሩ አስተያየት፣</u>

በኤጀንሲው ተቀጥረው በማስተማር ላይ ከሚገኙ የውጭ አገር ዜጎች ደመወዝ ያልተቀነሰ የሥራ ግብር ተቀንሶ ገቢ መደረግ እንደሚገባው ወይም ከግብር ነፃ ለመደረጋቸው ከሚመለከተው አካል የተፈቀደ መሆኑ ማስረጃ እንዲቀርብ በመጀመሪያው የኦዲት ሥራ ማጠናቀቂያ ወቅት ከሥራ አመራሩ ጋር በተደረገ ውይይት የተገለፀ ቢሆንም በበጀት ዓመቱ (ከሐምሌ/2009 እስከ ሰኔ/2010) ተቀናሽ ሳይደረግ ክፍያ መፈፀሙ ተረጋግጧል። መምህራኑ ከኤጀንሲው ጋር የገቡት ውል እና የሥራ ግዜያቸውን ጨርሰው መመለሳቸውን የሚገልፅ ማስረጃ ባለመቅረቡ የተሰጠው ምላሽ ተቀባይነት የለውም።

1.4.1 <u>ግኝት</u>፣ <u>አለአግባብ በጥሬ ገንዘብ የተፈፀመ ክፍያ፣</u>

በፌዴራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 አንቀፅ 6 ንዑስ አንቀፅ 4 በተሻሻለው መመሪያ ‹‹የመንግስት መስሪያ ቤቶች እስከ ብር 5,000.00 የሚደርሱ ወጪዎችን ቼክ መቁረጥ ሳያስፈልግ በገንዘብ ያዥ በኩል በጥሬ ገንዘብ መክፈል እንደሚችሉ ይገልፃል። ይሁን እንጂ በኤጀንሲው የውጪ ዜጎች ኮንትራት ሠራተኞች ደመወዝ ሲከፈል

በባንክ ሂሳብ በማስተላለፍ ክፍያ መፈጸም ሲገባው በተለያዩ የወጪ ማስመስከሪያዎች ከብር 5,000.00 በላይ ከሣጥን ወጪ ሆኖ በድምሩ ብር 1,633,462.02 በጥሬ ገንዘብ ክፍያ ተፈፅሞ መገኘቱ ተረጋግጧል ፡፡

1.4.2 ስጋት፣

የጥሬ ገንዘብ በመመሪያው መሠረት በአግባቡ ባለመጠበቁ ለብክነት ሊዳረግ ይችላል፡፡

1.4.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

ኤጀንሲው የሚገባቸው ውሎች ንብረትና ሀብት እንዲጠበቁ በማድረግ የተቋቋመለትን ዓላማ እንዲያሳካ የሚያደርጉ መሆን ይገባቸዋል፡፡ በመሆኑም የመንግስት ገንዘብ የክፍያ አፈፃጸም መመሪያን ተከትሎ ክፍያዎች እንዲፈፀሙ ቁጥጥርና ክትትል መደረግ ይኖርበታል፡፡

1.4.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፣

አብዘሃኛው የፊሊፒንስ ባለሙያዎች ክፍያ ሲሆን ከክፍያው ጋር በተያያዘው ውል መሰረት ሠራተኞቹ በአካል በኤጀንሲው ቀርበው እንዲከፈሉ ስለሚል በዚህ መሰረት ክፍያው ተፈጽሟል በተጨማሪም ኤጀንሲው የስልጠና ማዕከል በመሆኑ ብዙ ለሰልጣኞች አበል በካሽር ስም እየወጣ እንደሚከፈል እንዲታወቅና የመስሪያ ቤቱም የስራ ባህሪ መሆኑን እናረጋግጣለን፡፡

1.4.5 የኦዲተሩ አስተያየት፣

የመንግሥት ገንዘብ ለብክነት እንዳይጋለጥ ለማድረግ የወጣውን መመሪያ ኤጀንሲው ተግባራዊ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡ በመሆኑም የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ የውስጥ ቁጥጥር ሥርዐቱን በማጠናከር የተመደበለትን በጀት በአግባቡ በሰራ ላይ እንዲያውል የሥራ አመራሩ ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ ይገባዋል፡፡

1.5.1 ግኝት፣በጀት ዓመቱን ያልጠበቀ ክፍያ፣

የፌዴራል መንግሥት ገንዘብ ክፍያ ቁጥር 4 /2003 አንቀፅ 14 ንዑስ አንቀፅ 1 እና 2 የመደበኛና የካፒታል የሥራ ማስኬጃ ወጪዎች ሲፈፀሙ ወጪ ለሚደረግበት ተግባር በበጀት ዓመቱ የተያዘ ወይም ወጪውን ለመሸፈን ቀሪ በጀት መኖሩንና ወጪው በመሥሪያ ቤቱ ዕቅድ ውስጥ የተያዘና በጥሬ ገንዘብ ፍላጎት ዕቅድ ላይ የተካተተ መሆኑ ሳይረጋገጥ ክፍያ መፈጸም እንደማይገባ ያዛል፡፡ ይሁን እንጂ ኤጀንሲው በ10/01/09 በባንክ የወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 0832583 በወጪ የተያዘ ብር 747,327.01 በአዳማ ራስ ሆቴል ለተደረገ መስተንግዶ የተከፈለ እንዲሁም በቀን 28/02/09 በባንክ የወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር

0832627 በወጪ የተያዘና ከአኪያ ተሾመ ህትመት ሥራ ድርጅት የህትመት አገልግሎት ግዥ ለተፈፀመበት የተከፈለ ብር 88,480.43 በድምሩ ብር 835,807.44 በ2008 በጀት ዓመት ለተከናወነ ግዥ ክፍያ ተፈፅሞ ተገኝቷል ፡፡

1.5.2 ስጋት፣

የተፈቀደ በጀት ለታለመለት አላማ የማይውል ከሆነ የኤጀንሲው አመታዊ ዕቅድ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ሊፈጥር ይችላል፡፡

1.5.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

ኤጀንሲው በበጀት ዓመቱ የተፈቀደለትን በጀት በወቅቱ በሥራ ላይ ሊያውል ይገባል፡፡ ሂሳቡም በተከፋይ ተይዞ እንዲከፈል መደረግ ይኖርበታል፡፡ ለወደፊቱም ክፍያዎች በመንግስት ደንብና መመሪያ መሠረት እንዲፈፀሙ ክትትል መደረግ ይኖርበታል፡፡

1.5.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፣

የሥራ አመራሩ የተሰጠውን የማሻሻያ ሀሳብ ተቀብሎታል፡፡

1.6.1 ግኝት፣ተቀናሽ ያልተደረገ የተጨማሪ እሴት ታክስ፣

የፌዴራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 አንቀፅ 14 ንዑስ አንቀፅ 13 እና14 በቅድመ የገቢ ግብር እና በክፍያ ላይ የሚከፈልን የተጨማሪ እሴት ታክስ በተመለከተ በገገርው ተይዞ ስለሚከፈል የተጨማሪ እሴት ታክስ አፈጻጸም በወጣው መመሪያ መሠረት ተቀናሽ መደረግ እንደሚገባው ያዛል፡፡ ይሁን እንጂ መመሪያው ተግባራዊ መደረጉን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ ተክለይ ግደይ ጠቅላላ ስራ ተቋራጭ የአጥር ግንባታ፣ጥገና እና ግቢ ማስዋብ ስራ ከኤጀንሲው ጋር ውል ገብቶ ሥራው በመጠናቀቁ የመጨረሻ ክፍያ የተፈፀመ ሲሆን፣ ከተሰራው ጠቅላላ ስራ ብር 13,958,870.10 የተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 2,093,830.53 ተቀናሽ መደረግ ሲገባው ብር 1,463,212.66 በመቀነሱ ብር 630,617.86 ተቀናሽ ሳይደረግ ለተቋራጩ የተከፈለ መሆኑን፣

1.6.2 ስጋት፣

- ተቀናሽ መደረግ የሚገባው ታክስ ባለመቀነሱ የመንግሥት ገቢ ዝቅ ሊል ይችላል፡፡
- መንግሥት ሊያገኝ የሚገባው ገቢ በወቅቱ ላይሰበሰብ ይችላል፡፡

1.6.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

ለመንግስት ገቢ መደረግ የሚገባው ታክስ ከስራ ተቋራጩ ተመላሽ ተደርጎ ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ገቢ ሊደረግ ይገባል፡፡ ተቀናሽ መደረግ የሚገባው ታክስ በወቅቱ

እየተቀነሰ በተከፋይ እንዲያዝና ለሚመለከተው አካል ገቢ እንዲደረግ፣ ለወደፊቱም የዚህ አይነት አሰራር እንዳይከሰት ቁጥጥርና ክትትል መደረግ ይኖርበታል፡፡

1.6.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፣

የሥራ አመራሩ የተሰጠውን የማሻሻያ ሀሳብ ተቀብሎታል፡፡

1.7.1 ግኝት፣ በተከፋይ ያልተያዘ የመያዣ ሂሳብ፣

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ መንግስት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት ማኑዋል 3 ጥራዝ 1 መሠረት የመያዣ ክፍያ በግንባታ ውሉ መሠረት ግንባታው ተጠናቅቆ የመጨረሻ ርክክብ እስከሚፈፀም ድረስ ከየክፍያው በመቶኛ እየተሰላ ተቀንሶ የሚያዝ መሆኑን ይገልፃል። ይሁን እንጂ በመመሪያው መሰረት መፈፀሙን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ ተክላይ ግደይ ጠቅላላ ስራ ተቋራጭ ከኤጀንሲው ጋር የግንባታ፣ጥገና እና ግቢ ማስዋብ ስራ ውል ገብቶ ከሰራው ስራ የውል መያዣ ሂሳብ ተቀናሽ የተደረገ ሲሆን፣

- ከክፍያ ምስክር ወረቀት 01 በቀን 07/02/09 በባንክ ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 0832631 በወጪ የተያዘ ብር 239,577.83፣
- ከክፍያ ምስክር ወረቀት 02 በቀን 10/04/09 በባንክ ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 0831813 ብር 400,634.75፣
- ከክፍያ ምስክር ወረቀት 03 በቀን 13/08/09 በባንክ ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 243938 በወጪ የተያዘ ብር 522,151.02፣

በድምሩ ብር 1,162,363.60 ተቀናሽ የተደረገ ቢሆንም በተከፋይ ሂሳብ አለመያዙን ለማወቅ ተችሏል፡፡

1.7.2 ስጋት፣

- የኤጀንሲው የሂሳብ ሪፖርት ትክክለኛ ገፅታ እንዳያሳይ ያደርገዋል፡፡

1.7.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

የማስተካከያ ምዝገባ ቢከናወንም በ2009 በጀት ዓመት የሂሳብ መግለጫ ባለመካተቱ የበጀት ዓመቱን የተከፋይ ሂሳብ በማነስ ሪፖርት እንዲደረግ ምክንያት ሆኗል፡፡ ለወደፊቱም የመጨረሻ ርክክብ እስክፈፀም ድረስ ከእያንዳንዱ ክፍያ ተቀናሽ በማድረግ በተከፋይ እንዲመዘገብ እና በሂሳብ መግለጫ በተከፋይ የሂሳብ ሪፖርት እንዲካተት መደረግ ይኖርበታል፡፡

1.7.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፣

በወቅቱ ይህ ችግር ተፈጥሯል ነገር ግን የመጨረሻ ክፍያ በመስከረም ወር 2010 ሲከፈል በJV ተስተካክሎ የተሰራ መሆኑን እንገልጻለን።

1.7.5 የኦዲተሩ አስተያየት፣

በቀን 15/02/2010 በባንክ ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 497323 ለተቋራጩ የተከፈለው የመጨረሻ ክፍያ በወጪ የተያዘ መሆኑ በቀረበው የክፍያ ማስረጃ ቢረጋገጥም የመያዣ ሂሳብ በተከፋይ ሂሳብ መደብ 5061 አለመያዙ ተረጋግጧል፡፡

1.8.1 ግኝት፣በተገቢው የሂሳብ መደብ ያልተመዘገቡ ወጪዎች፣

ወጪዎች የሚመዘገቡት በነሐሴ 1999 ዓ.ም ባወጣው የኢትዮጵያ ፌዴራል መንግስት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መመሪያ መሰረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤

- በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 0832154 ለህንፃ ተቋራጮች የተከፈለ ቅድሚያ ክፍያ ብር 2,250,592.20 በሂሳብ መደብ 4251 መያዝ ሲገባው በሂሳብ መደብ 4253 ለዕቃ አቅራቢዎች ቅድሚያ ክፍያ ተብሎ መያዙን፡
- በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 0832138 ለማስታወቂያ አገልግሎት ወጪ የሆነ ብር 78,487.50 በሂሳብ መደብ 6213 ተይዞ መገኘቱን፣

በድምሩ ብር 2,329,079.70 በተገቢው የሂሳብ መደብ ሳይመዘገብ መገኘቱ ተረጋግጧል።

1.8.2 ስጋት፣

- ወጪዎች በተገቢው የወጪ ሂሳብ መደብ ተመዝግበው ሪፖርት ካልተደረጉ የኤጀንሲው የሂሳብ ሪፖርት ትክክለኛ ገፅታ ላያሳይ ይችላል።
- የሂሳብ አያያዙ የበጀት አጠቃቀም ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ያሳድራል።

1.8.3 የማሻሻያ ሀሳብ፤

የወጪዎች ምዝገባ ከመከናወኑ በፊት ትክክለኛ የወጪ ሂሳብ አርዕስታቸውን የጠበቁ መሆኑ መረጋገጥ ይኖርበታል።

1.8.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፣

የሥራ አመራሩ የተሰጠውን የማሻሻያ ሀሳብ ተቀብሎታል።

1.9.1 ግኝት፣ አለአግባብ የተከፈለ ደመወዝ ፣

የውጭ ሀገር መምህራን ቅጥርና የአስተዳደር መመሪያ በቀን 14/02/2001 በቁጥር መ-259/738/20 ክፍል ሁለት 2.2.12 የውጭ መምህራን ያላቸውን ሙያና የአካዳሚክ ደረጃ

መሠረት አድርጎ ሊከፈላቸው የሚገባው የደመወዝ መጠን በትምህርት ሚኒስቴር ለሙያ መስክ ደረጃ ከተቀመጠው ጣሪያ(scale) በላይ መሆን እንደሌለበት መመሪያው ይገልጻል፡፡ ይሁን እንጂ በኤጀንሲው በማገልገል ላይ የሚገኙት የኒውዝላንድ ዜጋ ሚስተር ፍራንክ ዊሊያምስ የሰለጠኑበትን ሙያ እና የትምህርት ደረጃ የሚገልፅ ማስረጃ ሳይቀርብ በኤጀንሲው ተቀጥረው ከ2002 ዓ.ም ጀምሮ በመስራት ላይ የሚገኙ መሆኑንና በበጀት ዓመቱ በድምሩ ብር 886,096.58 አለአግባብ የተከፈለቸው መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

1.9.2 <u>ስጋት፣</u>

- አለአግባብ ክፍያ በመፈፀሙ የኤጀንሲው በጀት ለቀደለት ዓላማ ላይውል ይችላል፡፡
- የወጣው መመሪያ ተግባራዊ ላይደረግ ይችላል፡፡

1.9.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

ተገቢው የትምህርትና የሙያ ማስረጃ ሳይኖራቸው ለሠራተኛው የሚከፈለው ደመወዝ እንዲቋረጥና የተከፈለው ተመላሽ እንዲደረግ እርምጃ መወሰድ ይገባዋል፡፡ የሠራተኛውን ቅጥር በተመለከተ የሥራ አመራሩ ተገቢውን ማብራሪያ መስጠት ይጠበቅበታል፡፡

1.9.4 <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

የተጠቀሱት ባለሙያ እንደ አሰልጣኝ ብቻ ሳይሆን የእንዱስትሪ ባለሙያ በመሆኑ እና በኢ.ፋፍ ድርጅት ድጋፍ የመጣ እና ብዙ ገንዘብ ሊገመት የሚችል ማሽን ድጋፍ ከሀገሩ ያስገባና አሁንም በማስገባት ላይ በመሆኑ በማዕከላችን ተጠቃሚ የሆነ ቢሆንም እንደ ሀገራችን ትምህርት ስርዓት ሳይሆን የእንዱስትሪው ሙያተኛ(meister) በመሆኑ በቂ መረጃ በተጠየቀው መሰረት እና መቅረብ አልቻለም። ነገር ግን ከዚህ በፊት ሲቀጠር ከcv ጋር የገባ የመሰለኝ የሚል ምላሽ ብቻ ነው ያገኘሁት፡፡ አሁን ግን የተጀመረው የትራክተር ምርት እስከምጠናቀቅ የትራክተሩ እና ክፍያው ሁኔታ ለከፍተኛ አመራር ቀርበው በትምህት ሚኒስተር እንዲፀድቅ የሚናደርግ ይሆናል የሚል አስተያየት አለኝ፡፡

1.9.5 <u>የኦዲተሩ አስተያየት፣</u>

የባለሙያውን የትምህርት ደረጃና የቅጥር ሁኔታ በተመለከተ የኤጀንሲው ሥራ አመራር ተገቢውን ማብራሪያ መስጠት እንደሚገባው በቀረበው የማሻሻያ ሀሳብ ቢገለፅም በኦዲቱ ወቅት ከተሰጠው የተለየ ምላሽ አለመሰጠቱንና ማስረጃም አለመቅረቡን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

2 የተሰብሳቢ ሂሣብ፣

2.1.1 ግኝት፤ በደንቡ መሠረት በወቅቱ ያልተወራረደ ተሰብሳቢ ሂሳብ፤

በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀጽ 32 እንዲሁም በፌዴራል የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 4/2003 መሰረት ለውሎ አበልና ለመጓጓዣ የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ ሠራተኛው ሥራውን አጠናቆ ከተመለሰ በኂላ በሰባት የሥራ ቀናት ውስጥ፤ በመመሪያ ቁጥር 5/2003 መሰረት ደግሞ ለግዥ የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ በሰባት የሥራ ቀናት ውስጥ መወራረድ እንዳለበት ያዛል፡፡ ይሁን እንጂ ተሰብሳቢ ሂሳብ በመመሪያው መሠረት በወቅቱ የሚወራረድ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

- በሂሣብ መደብ 4201 የተያዘና ለልዩ ልዩ ቅድሚያ ክፍያ የተሰጠ ብር 26,766.85 ከ 2 ዓመታት በላይ፡
- በሂሣብ መደብ 4203 የተያዘ እና ለሠራተኞች የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ ብር 74,805.89 ከ1 ዓመት በላይ፣ብር 271,103.31 ከ4 ዓመታት በላይ፣ብር 28,623.48 ከ2 ዓመታት በላይ፣ ብር 17,930.10 ከ 8 ወራት በላይ፣ እንዲሁም ብር 4,511.25 ከ4 ወራት በላይ ከ3 ወራት በላይ፤ በድምሩ ብር 396,974.03፣
- በሂሣብ መደብ 4210 የተያዘ እና ለመንግሥታዊ ድርጅቶች የተከፈለ ብር 611,588.95 ከ 3 ዓመት በላይ፣
- በሂሣብ መደብ 4211 የተያዘ እና ለግዥ ቅድሚያ ክፍያ የተሰጠ ብር 158,700.00 ከ2 ዓመታት በላይ፣
- በሂሣብ መደብ 4274 የተያዘ ለልዩ ልዩ ቅደሚያ ክፍያዎች ወጪ የሆነ ብር 48,951.81 ከ 2 ዓመት በላይ፣

በድምሩ ብር 1,242,981.64 በደንቡና በመመሪያው መሠረት በወቅቱ ሳይወራረድ ተገኝቷል፡፡

2.1.2 ስጋት፣

በቅድሚያ ክፍያ ወጪ የተደረገው ሂሳብ በጊዜ ገደቡ ውስጥ አለመወራረዱ የመንግስት ገንዘብ በግለሰቦች፣ በመ/ቤቶችና ድርጅቶች ተይዞ እንዲቆይ የሚያደርግ ከመሆኑም በተጨማሪ ሂሳቡ ወደማይወራረድበት ደረጃ ሊደርስ ይችላል፡፡

2.1.3 የማሻሻያ ሀሳብ፤

በወጣው የሂሳብ አያያዝ ሥርዐት መመሪያና ደንብ መሰረት ተሰብሳቢ ሂሳቦች ተገቢው ማስረጃ ቀርቦላቸው በወቅቱ እንዲወራረዱ መደረግ ይኖርበታል፡፡

2.1.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፣

የሥራ አመራሩ የተሰጠውን የማሻሻያ ሀሳብ ተቀብሎታል፡፡

2.2.1 ግኝት፣ ባልተለመደ የሂሳብ ሚዛን የተመዘገበ ተሰብሳቢ ሂሳብ፣

የገቢና የወጪ ሂሳቦች የሚያዙትና የሚመዘገቡት የገ/ኢ/ል/ሚ/ር ነሐሴ 1999 ዓ.ም ባወጣው የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መመሪያ መሰረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በተሰብሳቢ የሂሳብ መደብ 4203 የተያዘና ለሠራተኞች የተሰጠ የቅድሚያ ክፍያ ብር 148,732.36 እንዲሁም በሂሳብ መደብ 4253 የተያዘ ለእቃ አቅራቢዎች የተከፈለ የቅድሚያ ክፍያ ብር 3,721,426.36 በተቀፅላ የሂሳብ ቋት (ሌጀር) ባልተለመደ የሂሳብ ሚዛን (ክሬዲት) ተመዝግቦ መገኘቱ ታውቋል፡፡

2.2.2 ስጋት፣

የሂሳብ ሌጆሮች ትክክለኛውን የሂሳብ ሚዛን ማሳየታቸው ካልተረጋገጠ የሂሳብ መገለጫዎቹ የኤጀንሲውን የፋይናንስ አቋም በትክክል ላይገልጹ ይችላሉ፡፡

2.2.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

የተሰብሳቢ ሂሳብ አያያዝ እና አመዘጋገብ በመመሪያው መሠረት ተግባራዊ እንዲደረግ እና በሪፖርት ዝግጅት ወቅት የሂሳብ ሌጆሮች ትክክለኛውን የሂሳብ ሚዛን ማሳየታቸው እንዲረጋገጥ ክትትል እና ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል፡፡

2.2.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፣

የሥራ አመራሩ የተሰጠውን የማሻሻያ ሀሳብ ተቀብሎታል፡፡

3. የተከፋይ ሂሳብ፣

3.1.1 ግኝት፣ በወቅቱ ለባለመብቱ ያልተከፈለ ሂሳብ፣

የተከፋይ ሂሳቦች ለሚመለከታቸው አካላት በወቅቱ የተከፈሉ ወይም የተወራረዱ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

- በሂሣብ መደብ 5002 የተያዘ እና ለመ/ቤቱ ሠራተኞች የሚከፈል ብር 1,830,247.98 ከ2 ዓመታት በላይ፣
- በሂሣብ መደብ 5005 የተያዘ የደመወዝ ተከፋይ ብር 121,680.27 ከ3 ዓመት በላይ፣
- በሂሣብ መደብ 5006 የተያዘ እና ከተከፋይ ሂሳብ ተቀናሽ (ዊዝሆልዲንግ) ታክስ ብር 597,857.60 ከ3 ዓመት በላይ፣

- በሂሣብ መደብ 5028 የተያዘ እና ለተለያዩ ድርጅቶች የሚከፈል ብር 544,806.55 ከ3 ዓመት በላይ፣ ብር 5,841.00 ከ2 ዓመት በላይ፣ በድምሩ ብር 550,647.55
- በሂሣብ መደብ 5054 በልዩልዩ የመያዣ ሂሳብ የተያዘ ብር 3,043,919.43 ከ2 ዓመት በላይ፣ ብር 616,962.78 ከ1 ዓመት በላይ፣ በድምሩ ብር 3,660,882.21

በጠቅላላ በድምሩ ብር 6,761,315.61 ለባለመብቱ ሳይከፈል ተገኝቷል፡፡

3.1.2 ስጋት፣

የተከፋይ ሂሳብ ለባለመብቱ ድርጅት፣ መ/ቤት ወይም ግለሰብ በወቅቱ አለመተላለፉ ገንዘቡ ለታቀደለት ዓላማ እንዳይውል ሊያደርግ እና በበጀት አጠቃቀም ላይም ተጽዕኖ ሊያሳድር ይችላል፡፡

3.1.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

ተከፋይ ሂሳቦች በወቅቱ ለሚመለከተው አካል መከፈል ይኖርባቸዋል፡፡ ለወደፊቱም በተከፋይ ሂሳብ ላይ አፋጣኝ እርምጃ እንዲወሰድ ቁጥጥርና ክትትል መደረግ ይኖርበታል፡፡

3.1.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፣

የሥራ አመራሩ የተሰጠውን የማሻሻያ ሀሳብ ተቀብሎታል፡፡

3.2.1 ግኝት፣ ባልተለመደ የሂሳብ ሚዛን የተመዘገበ ተከፋይ ሂሳብ፣

የገቢና የወጪ ሂሳቦች የሚያዙትና የሚመዘገቡት የገ/ኢ/ል/ሚ/ር ነሐሴ 1999 ዓ.ም ባወጣው የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መመሪያ መሰረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በተከፋይ የሂሳብ መደብ 5002 የተያዘ ለሠራተኞች የሚከፈል ብር 44,766.92 በተቀፅላ የሂሳብ ቋት (ሌጀር) ባልተለመደ የሂሳብ ሚዛን (ዴቢት) ተመዝግቦ መገኘቱ ተረጋግጧል፡፡

3.2.2 ስጋት፣

የሂሳብ ሌጀሮች ትክክለኛውን የሂሳብ ሚዛን ማሳየታቸው ካልተረጋገጠ የሂሳብ መግለጫዎቹ የኤጀንሲውን የፋይናንስ አቋም በትክክል ላይገልጹ ይችላሉ፡፡

3.2.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

የተከፋይ ሂሳብ አያያዝ እና አመዘጋገብ በመመሪያው መሠረት ተግባራዊ እንዲደረግ እና በሪፖርት ዝግጅት ወቅት የሂሳብ ሌጀሮች ትክክለኛውን የሂሳብ ሚዛን ማሳየታቸው እንዲረጋገጥ ክትትል እና ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል፡፡

3.2.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፣

የሥራ አመራሩ የተሰጠውን የማሻሻያ ሀሳብ ተቀብሎታል፡፡

4.በጀት፣

4.1 ግኝት፣ ሥራ ላይ ያልዋለ በጀት እና ከበጀት በላይ የወጣ ፤

በፌዴራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 6/2 መሠረት የበጀት ዝውውር ወይም ተጨማሪ በጀት ካልተፈቀደ በስተቀር ለአንድ የመንግስት መ/ቤት በሂሳብ መደብ ተለይቶ ከተፈቀደው በጀት በላይ ወጪ መፈፀም እንደማይቻል ያስረዳል፡፡ በተጨማሪም በፌዴራል መንግሥት የበጀት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 2/2003 እና በፋይናንስ አስተዳደር ደንብ ቁጥር 190/2002 ክፍል 3 አንቀጽ 12 መሠረት መ/ቤቶች የተመደበላቸውን በጀት በአግባቡ በሥራ ላይ ሊያውሉ እንደሚገባቸው ይገልፃል፡፡ ይሁን እንጂ የኤጀንሲው የበጀት አስተዳደር፣ አጠባበቅ እና አጠቃቀም መመሪያን የተከተለ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

- ለመደበኛ ወጪ ለየፕሮግራሞቹ የተፈቀደው በጀት ሥራ ላይ ከዋለው ጋር ሲነጻጸር በየሂሳብ መደቦቹ ከ10% በላይ ብር 18,166,762.83 ሥራ ላይ ያልዋለ መገኘቱን፣
- ለካፒታል ወጪ ለየፕሮግራሞቹ የተፈቀደው በጀት ሥራ ላይ ከዋለው ጋር ሲነጻጸር ብር 272,393.87 ከበጀት በላይ ወጪ መደረጉን እንዲሁም በየሂሳብ መደቦቹ ከ10% በላይ ብር 111,634,928.30 ሥራ ላይ ያልዋለ መገኘቱን፣ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

4.2 ስጋት፣

- በበጀት ዓመቱ ተራፊ በጀት መገኘት በሌሎች መ/ቤቶች ሊሠራበት የሚችለውን በጀት በኤጀንሲው ስም ተይዞ እንዲቆይ ያደርጋል፡፡
- የተፈቀደው በጀቱ በዕቅዱ መሠረት ተግባራዊ አለመደረጉ የኤጀንሲውን ዓመታዊ የሥራ ውጤት ዝቅ የሚያደርግ ከመሆኑም በተጨማሪ የበጀት ዕቅዱን ትክክለኛነት ላያመለክት ይችላል፡፡

4.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

ሥራ ላይ ያልዋለ በጀትን በተመለከተ በተሰጠው ምላሽ በተለያዩ ምክንያቶች ሥራዎች ባለመሰራታቸው፣የታቀዱ ሥልጠናዎችና ስብሰባዎች ባለመካሄዳቸው እንዲሁም የሥራ እና የኪራይ ውሎች ባለመፈፀማቸው በየሂሳብ መደቡ የተፈቀደው በጀት በሥራ ላይ አለመዋሉ የተገለፀ ቢሆንም ኤጀንሲው ለሚያከናውናቸው ተግባራት ሊውል የሚችል በጀት የመ/ቤቱን

የስራ ባህርይ መሠረት በማድረግ እንዲፈቀድ ባለመደረጉ ሳይሰራበት ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም ኤጀንሲው በጥናት ላይ የተመሰረተ ዕቅድ በማዘጋጀት የሚፈቀድለትን በጀት በአግባቡ በሥራ ላይ እንዲውል ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡

ከበጀት በላይ ወጪ የተደረገውን በተመለከተ በተሰጠው ምላሽ ከተፈቀደው በላይ ክፍያ የተፈፀመው የደመወዝ ጭማሪ በመደረጉ እና የውሀ እና የሌሎች ፍጆታዎች ወጪ ከፍተኛ በመሆኑ ወጪ መደረጉ የተገለፀ ቢሆንም ለተደረገው የደመወዝ ጭማሪ ለሚመለከተው አካል የተጨማሪ በጀት ጥያቄ በማቅረብ ወጪውን መሸፈን ሲገባ ባልተፈቀደ በጀት ክፍያ መፈፀሙ የተፈቀደለትን በጀት በአግባቡ አለመጠቀሙን የሚያመለክት በመሆኑ የሥራ አመራሩ ተገቢውን ማብራሪያ ሊስጥበት ይገባል፡፡

4.4 <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

የሥራ አመራሩ የተሰጠውን የማሻሻያ ሀሳብ ተቀብሎታል፡፡

5. <u>ንብረት፡</u>

5.1 <u>የኤጀንሲውን የንብረት አያያዝና አጠባበቅ በተመለከተ</u>

የኤጀንሲው የንብረት አመዘጋገብ፣አያያዝ እና አጠባበቅ በአዋጅ ቁጥር 649/2001 እና በንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 6 ንኡስ አንቀጽ 1 ፊደል ተራ ሐ የመንግስት መስሪያ ቤቶች የንብረት ተጠቃሚ ሰዎችን ካርድ/USC/ መያዝ እንዳለባቸው፣ ክፍል ሶስት አንቀጽ 9 ፊደል ተራ ሀ የስቶክ ቁጥጥር አስተማማኝ ተገቢና መሠረታዊ መዛግብቶችን መሠረት ያደረገ መሆን እንደሚገባው፣አንቀጽ 8 የመንግስት መስሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ የመንግስት ንብረት ኢኮኖሚያዊና ውጤታማ በሆነ መንገድ አገልግሎት እንዲሰጥ ተገቢ የጥገናና እንክብካቤ ሥርዓት መዘርጋት ያለበት መሆኑ ተገልጿል፡፡ ይሁን እንጂ የኤጀንሲው የንብረት አስተዳደር፣ አያያዝና አጠባበቅ በወጣው መመሪያ መሠረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

<u>ቋሚና አላቂ ዕቃዎችን በተመለከተ፣</u>

በድምሩ ብር 1,583,800.ዋጋ ያላቸው ለተጠቃሚዎች የተሰጡ የተለያዩ ንብረቶች የንብረት ተጠቃሚ ካርድ፣ ስቶክ ካርድና ቢን ካርድ ያልተቋቋመለቸው መሆኑ ታውቋል፡፡

ተ ቁ	ቀን	የንብረት ገቢ/የንብረት ወጪ ደረሰኝ ቁጥር	የዕቃው ዓይነት			ጠቅላለ ዋጋ
1	17/12/08	MO 22-437577	ባኖሻ ላፕቶፕ S/N-PFOADUMTM 80-E50220UE	01	ይታየው ደሲል	17,588.99

ተ ቁ	ቀን	የንብረት ገቢ/የንብረት ወጪ ደረሰኝ ቁጥር	የዕቃው ዓይነት			ጠቅላለ ዋጋ
			MO-PF9xs 707011			
2	05/3/09	MO 22-437963	የኃላፊ ጠረጴዛ	01		17,463.00
3	27/6/09	MO 22-926624	Photo Copy Machine S/N-6E0009395	01	አምላኩአለባቸው	15,554.90
4	26/7/09	MO 22-927003	Teshkerkari wonber	01	ብርሃኑ ታደሰ	2,298.85
5	16/8/09	MO 19-570270	Dancing Li-V	1000		202,000.00
6	01/9/09	MO 19-0031865	300KVA Generator Closed Type	01		1,273913.04
7	15/9/09	MO 19-570288	Nafta	400		6,540
8	9/10/09	MO 19-843163	UHU	25		540.00
9	28/10/09	MO 19-843186	Toner Hp leser jet 2600	02	ሙሉ አስማረ	26,680.00
10	28/10/09	MO 22-92046	LCD projecter	01	አሰፋ ኪዳነ	16,004.00
11	29/10/09	MO 22-92047	Graínder Machinc 115MM	02	መስፍን አየለ	5,217.40
			ድምር			1,583,800.18

- ከተራ ቁጥር 1 እስከ 4 እና ተራ ቁ 10 የንብረት ተጠቃሚ ካርድ ያልተቋቋመላቸው፣
- ከተራ ቁጥር 5 እስከ 8 ስቶክና ቢን ካርድ ያልተቋቋመላቸው፣
- ተራ ቁ. 9 እና 11 ስቶክና ቢን ካርድ እንዲሁም የንብረት ተጠቃሚ ካርድ አልተቋቋመም፤

➢ ብር 223,492.491 ዋጋ ያላቸውን ንብረቶች ሳይመልሱ የተረከቧቸው ሠራተኞች ኤጀንሲውን የለቀቁ መሆኑ ተረጋግጧል። ዝርዝሩ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ተ.ቁ	ስም	የስራ ክፍል	የወስዱት የዕቃ ዓይነት	ብዛት	የገንዘብ መጠን
1	አቶ ተስፋዬ አድነው	ከፍተኛ ፕሮጀክት ባለሙያ	ካልኩሌተር ቶሽባ ላፕቶፕ	01 01	12,379.77
2	አቶ ካሐሰ ገ/መድህን	አማካሪ	ሰምሰንግ ሞባይል የስም እና የስልጣን ቲተር ላፕቶፕ ዴል ሲዲአምአ	01 02 01 02	35,733.02
3	አቶ አዲሱ ፀሀይ	የሙያ ባቃት ምዘና ቡድን መሪ	ላፕቶፕ ኮምፒተር ቪዲዮ ካሜራ ፎቶ ካሜራ	01 01 01	33,789.01
4	አቶ ተካልኝ ዘሪሁኝ	ኢንተርፕሩነር ሽፕ	የፎቶ ካሜራ ላኖቫ ላፕቶፕ	01 01	24,798.35
5	አቶ አሸናፊ ገ/መስቀል	ቴክኖሎጂ ፋብሪኬሽን	ዲጂታል ካሜራ	01	4,440.05
6	አቶ ገመቺስ ኦልቃ	ቴክኖሎጂ ቡድን	ላኖቫ ላፕቶፕ ዩፒኤስ	01 01	31,636.24
7	አቶ ናታናኤል መንግስቱ	ኢንተርፕሩነር ሽፕ	ላኖቫ ላፕቶፕ	01	17,496.99
8	አቶ ቤተማሪያም	ቴክኖሎጂ ፋብሪኬሽን	ኤችፒ ላፕቶፕ ዩፒኤስ	01 01	31,636.00
9	ወ/ሮ ራሄል ሰለሞን	ሙያ ደረጃ	ላኖቫ ላፕቶፕ	01	17,496.99

10	አቶ ደሳለኝ	ኢ/ኤ/ቴ/ ሽግግር	ኤችፒ ላፕቶፕ	01	13,565.845
			ድምር		223,492.491

- ➢ በኤጀንሲው የአላቂ ንብረት ግምጃ ቤት ውስጥ ዕቃዎቹ በአይነት በአይነታቸው ተለይተው እንዲቀመጡ አለመደረጉን፣
- ➢ በቋሚ ንብረት ግምጃ ቤት ውስጥ ቋሚና አላቂ ንብረቶች ተቀላቅለው በአንድ መጋዘን ውስጥ የተቀመጡ መሆኑ፡፡ ለምሳሌ ኮምፒውተሮች፣ፋይሊንግ ካቢኔቶች፣ፕሪንተሮች፣ ሪሲቨሮች፣ የመስተዋት ማጽጃ፣ ላርጎ ፈሳሽ ሳሙና፣ ፖስተሮች የሚገኙ መሆኑ፣

- ➢ 21 ያገለገሉ አሮጌ ተሽከርካሪ ወንበሮች፣7 ተሽከርካሪ ያልሆኑ ወንበሮች፣4 የቢሮ ጠረጴዛዎች 2 የሚገጣጠሙ ኮመዲኖዎች፣1 የኮምፒውተር ማስቀመጫ 1 የፋይል መደርደሪያ 7 የብረት ወንበሮች በኤጀንሲው የምህንድስና ብቃት ማዕከል ግቢ ውስጥ ከመጋዘን ውጭ ባለው ወለል ላይ የሚገኙ መሆኑ ታውቋል፡፡

<u>የኤጀንሲውን የተሽከርካሪዎች አያያዝ በተመለከተ፣</u>

- ➢ የሰሌዳ ቀጥሩ 4-15398 እና የሰሌዳ ቀጥሩ 4-15399 ቶዮታ ኮምፓክት መኪናዎች በብልሽት ምክንያት ለ1 ዓመት መቆማቸው፣እንዲሁም የሰሌዳ ቀጥሩ 4-15385 ቶዮታ ፒክ አፕ ለወራቶች ሳይሰራ መገኘቱን፣

- ➢ የሰሌዳ ቀጥሩ 4-14011 የሆነ ቶዮታ ሀርድ ቶፕ መኪና በሊብሬው ላይ የሚገኝ ሻንሲ ቁጥር JTEEB71J-70700383 የተመዘገበ ሲሆን በተሽከርካሪው ላይ የሻንሲ ቁጥሩ JTEEB71J-707003833 በመሆኑ በተሽከርካሪውና በሊብሬው መካከል የመረጃ ልዩነት የታየ መሆኑ፡

5.2 <u>ስጋት፣</u>

- ተገቢው የንብረት ምዝገባ እና አያያዝ ሥርዓት ተግባራዊ ባለመደረጉ ኤጀንሲው ለተጨማሪ ወጪ ሊዳረግ ይችላል፡፡
- በመንግሥት ውስን ሀብት የተገዙት ንብረቶች ለግለሰቦች ጥቅም በመዋላቸው የመንግሥት ገንዘብ ለታቀደለት ዓላማ ሳይውል ይችላል፡፡
- በንብረት አስተዳደር አዋጅና መመሪያ መሠረት ንብረቶች በአግባቡ ባለመጠበቃቸው ለብክነት ሊዳረጉ ይችላሉ፡፡

5.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

ኤጀንሲው የወጣውን የንብረት አያያዝና አጠባበቅ መመሪያ ተግባራዊ በማድረግ፣

- ስቶክ ካርድና ቢን ካርድ ለሁሉም ቋሚና አላቂ ዕቃዎች መደራጀት ይኖርበታል፡፡ በተጨማሪም ለንብረቱ ተጠቃሚዎች ካርድ/USC/ እንዲቋቋም እና በአገልግሎት ላይ በሚገኙበት ግዜ በአግባቡ በሥራ ላይ መዋላቸው ክትትል እና ቁጥጥር ሊደረግበት ይገባል፡፡
- ለቢሮ አገልግሎት እንዲውሉ የተሰጡ ቋሚ ዕቃዎች ከሚመለከታቸው ሠራተኞች ተመላሽ እንዲደረጉ ተገቢው ክትትል መደረግ ይኖርበታል፡፡
- ቋሚና አላቂ ዕቃዎች ለብልሽት እንዳይዳረጉ ተለይተው እንዲጠበቁ መደረግ ይገባዋል፡፡
- ተጠግነው አገልግሎት መስጠት የሚችሉትን ንብረቶች እንዲጠገኑ ማድረግና አገልግሎት መስጠት የማይችሉትን በመመሪያው መሠረት እንዲወገዱ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡
- ለተሽከርካሪዎቹ በመመሪያው መሠረት ጥገና እንዲደረግላቸውና አገልግሎት መስጠት እንዲችሉ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡
- የመረጃ ልዩነት ያለው በተሽከርካሪው ሊብሬ እና በመኪናው ላይ የሚገኘው ሻንሲ በትክክል እንዲናበብ ልዩነቱን ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን እንዲስተካከል ማድረግ ይገባል፡፡

5.4 <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

የሥራ አመራሩ የተሰጠውን የማሻሻያ ሀሳብ ተቀብሎታል፡፡

6. <u>ልዩ ልዩ</u>

6.1 <u>ግኝት በ2008 ኦዲት ግኝቶች ላይ ስለተወሰደ የእርምት እርምጃ፣</u>

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ማቋቋሚያ አዋጅን ለማሻሻል በወጣ አዋጅ ቁጥር 982/2016 ክፍል አምስት አንቀጽ 17/3 መሰረት ተመርማሪ መሥሪያ ቤቶች በፌዴራል ዋናው ኦዲተር በተላኩ ሪፖርቶች በተገለፁ ግኝቶች ላይ ተገቢውን የእርምት እርምጃ እንዲወስዱ በተሰጡ የማሻሻያ ሃሣቦችና አስተያየቶች መሠረት ከ15 ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ እርምጃ የመውሰድ ግዴታ አለባቸው፡፡የወሰዱትን እርምጃ እና ለመውሰድ ካልቻሉ ምክንያቱን በመግለጽ ለፌዴራል ዋናው ኦዲተር መሥሪያ ቤት ከላይ በተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ውስጥ ማሳወቅ አለባቸው፡፡በዚሁ መሰረት የኤጀንሲውን የ2008 በጀት ዓመት ኦዲት ሪፖርት በተሰጠው አስተያየት መሠረት እርምጃ ስለመወሰዱ ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣

- ኤጀንሲው ለሚፈፅማቸው ክፍያዎች ተገቢው የወጪ ማስረጃ ቀርቦላቸው በወጪ እንዲመዘገቡ የሚደረግ መሆኑን ለማረጋገጥ በናሙና ኦዲት ሲደረግ፤በቀን 30/2/2008 በባንክ ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 581268 አሥራ አንድ የኤጀንሲው ሠራተኞች ለመሠረታዊ የአሰራር ማሻሻያ (BPR)ሥልጠና በፊሊፒንስ ከጥቅምት 6-ጥቅምት 16/2008 ለሚቆዩበት ለውሎ አበል ለእያንዳንዳቸው ከተከፈላቸው 1,550 ዶላር ወይም ብር

368,320.01 ውስጥ ለመኝታና ለቁርስ የተከፈላቸውና በሚያቀርቡት የክፍያ ማስረጃ መወራረድ የሚገባው(USD 200*11)2,200.00 ወይም ብር 45,860.98 የወጪ ማስረጃ ሳይቀርብለት በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡

6.2 <u>ስጋት፣</u>

የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት ድክመቶች ሊቀረፉ አይችሉም፡፡

6.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

በኤጀንሲው የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች እንዲቀረፍ ብሎም ግልፅኝነትና ተጠያቂነት እንዲሰፍን የኤጀንሲው ሥራ አመራር በኦዲት በሚሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሠረት የእርምት እርምጃ በመውሰድ የበኩሉን አስተዋፅኦ ሊያበረክት ይገባል፡፡

6.4 <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

የሥራ አመራሩ የተሰጠውን የማሻሻያ ሀሳብ ተቀብሎታል፡፡

በመጨረሻም ለተደረገልን መልካም የሥራ ትብብር እናመሰግናለን፥